# ኢትዮድያዊነት ማለት ሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድህን ማለት ነው።
# አፍሪካዊነት ማለትም ብላቴ ጌታ ሎሬት ጸጋዬ/ ገመድህን ማለት ነው

ከሥርጉተ ሥላሴ 22.02.2017 (ዙሪክ – ሲዊዘርላንድ)



ሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድህን

„ጥበብ፡ ፈጽማ፡ የጎላች፡ ናት፡ ሥርዓቷም፡ አይልፍም፡ የሚወዷትም፡ ሰዎች፡ ፈጥነው፡ ያዋታል፡ የሚፈልጓትም፡ ሰዎች፡ ያገኙአታል። ለሚወዷት፡ ሰዎች፡ ትደርስላቸዋለች፡ አስቀድማም፡ ትገለጥላቸዋለች። በደጃፉ፡ ስትጠብቀው፡ ሁልጊዜ፡ እርሱ፡ ያገኛታል፡ ወደርስዋ፡ የሚገሠግሥ፡ ሰው፡ አይደክምም።  እርስዋን፡ ማሰብ፡ የውቀት፡ ፍፃሜ፡ ነውና። ፈጥኖ፡ ስለርሷ፡ የሚተጋ፡ ሰው፡ ያለ፡ ሃዘን፡ ይኖራል።“ (መጽሐፈ ጥበብ ምዕራፍ 6 ቁጥር 12 እስከ 16)

ይድረስ ለቅኔው ልዑል ለብላቴ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን  – ሰማይ ቤት።

አዬ … ቀን ይሄዳል – ይጓዛል። እኛን አስቀምጦ እሱ ማንአለበት ይነጉዳል፥ ይተማል፥ መጪ ይላል። ጋሼ ጸጋዬን በሥጋ ያጣንበት ወርኃ ዬካቲት። ወርኃ የካቲት የሰማዕታት መታሰቢያ … ዛሬ እስኪ ትንሽ ስለ ቅኔው ልዑል ስለብላቴ መንፈሴ ያሰኘውን ባሻው መንገድ ይል ዘንድ ወደድኩ። እንዲህና እንዲያ …

ማን እንደአንተ ጋሼ ጸጋዬ በንጽህና እና ቅድስና **ኢትዮድያን ከውስጧ ሆኖይቃኘላት።** በመሆን የከበርክ – ስለእሷ እሷን ሆነህ፤ እሷን **ጠጥተህ ተመገብኸ**
**የኖርክ ሩቅ አሳቢ፤ የተበተነን መንፈስ ሰብሳቢ፤** የአፍሪካዊነት ልዑቅ – ሊቅ፤ የሰው ዘር አፍቅሮተ ትንግርትህ  – ቀንዲልነቱ የምዕተ ዓመታት ህትምት ነው **ቤተ – መዘክር**። ደጉ የቅኔው ግሥ ፤ ሩህሩሁ ሰዋሰው፤ ጌታ ብላቴ ሎሬት ጸጋዬ ገ / መድህን፤ እንደ ስምህ በምግባርህ የከበርክ የእናት ኢትዮጵያ  **የውብ ቀን መርህ** ።
መሆንን በመሆን እንዝርት ፈትለህ ለሰንደቅህ ልዕልና ነበርክ **ነገረፈጅ**። ባለችሎት ቢኖር፤ የመንፈሱ አቅም ያልተንኮላሼ ቢገኝ፤ ያ … ንዑድ መንፈስህ ምንኛ **የኢትዮድያዊነት የፊደል ገበታ በሆነ ነበር?** አልፈህ ተርፈህ ስለ እማማ አፍሪካ የተጨነክ – የተጠበብክ **የድርጊት አንበል**ነበርክ።

ስለእያንዳንዱ ቅንጣት አመክንዮ በጉዳዩነት የያዝክ **ዝልቅ ሰው** ነበርክ። ትናትን ከዛሬ፤ ዛሬን ከነገ ያዋደድክ ዬጥበብ ንጡር ናሙና። አንተ፤ አንተማ ለእኔ **ህዝብ ነበርክ።** መቼ ቀንጣ እንደእኔ ነበርክና። በሕዝብ ውስጥ ሆነህ ስለህዝብ የኖርክ፤ **የህዝብ የፍቅር አውደ ምህረት።**ሞት ክፉ ሳያራራ ነጠቀን እንጂ። **አንተ ራስህ እኮ ሀገር ነህ። የኢትዮጵያዊነት <u>እንደራሴ! የአፍሪካዊነት ጭንቅላት።</u>** የጥቁርነት ዕንቁነት በፀዳለ ትውፊት በሙሉዑ ሥነ ባህሪ ያበራህ፤ ኢትዮጵያን ያደመቅህ፤ ያስዋብክ፤ ያፈካህ **የዘለዓለም ብርሃን።** ውስጥህን ሳትሳሳ፤ ለእናትህ ያለተቀናቃኝ ንጹህ **ልብህን የሸለምክ፤** ብሩካዊ መንፈስህን ያለ የግለኝነት ጣውንትነት ለልዕልት ኢትዮጵያ ፍቅር ያስገዛህ – **ቀንዲል።** እናት ሐገራችን ኢትዮጵያ ከፍ ብላ ስትታይ፤ ሞገሷ ሲጎመራ፤ ብቃቷ በአለም አደባባ ሲናኝ፤ ልጆቿ ሲወጡላት ነበር የሐሴትህምንጭ። ለዚህም በምድር በኖርክባቸው ዘመንህ ሁሉ ሁለመናዋ ነበርክ። ክብሯ፤ ሞገሷ፤ ማማዋ፤ ጸዳሏ፤ **ዘመኗ!** ዋስ ጠበቃዋ፤ ዋቢዋ።
ትውልድ አልፎ ትውልድ መተካቱ ተፈጥሯዊ ዶግማ ቢሆንም፤ አንተን፤ ስለእናት ሀገርህ ያለህ መወድሳዊ ያን ረቂቅ ቅዱስ መንፈስህን ግን የሚተካ አልተገኘም። ኢትዮጵዊነት እንደ ቁጥር ትምህርት በመደመርና በመቀነስ፤ ወይንም በመዳበል፤ ወይንም እንደ ተገጣጣሚ ዕቃ ተወልቆ እንደሚገጣጠም የጋራጅ ብረታ ብረት፤ ወይንም እንደ ጭቃ ተጠፍጥፎ ወይንም ተንቦልቡሎ እንደሚሰራ ጉሽጉሻ ሆነ ዕሳቤው ሁሉ።

ይህን ስልህ ግን ቅርጹ ተሸራርፎም ቢሆንም አለ – **የተሰወረብን ይዘቱ ነው።** የተሰወረው ዬፍጥረተ ነገሩ ንጥረ – ቅመም የግንዛቤው ጥልቀት ግልፍተኛ መሆኑን ነው። ኢትዮጵያዊነት ማሰሪያው በዛ። ምሳሩም አዬለ።በቅድመ ሁኔታ ገመድ ተተበተበ። ይለፋ አንተ ከምታውቀው **ከጸዳ የዕውነት ዕሴት መነሳት ተሳነው።**
ይሄውልህ የእኛ ግርማ እንዲህ የሆነበት ነገረ ምክንያቱ አሰዋወሩ ዬፍጥረተ ነገሩ ንጥረ ቅመም – የግንዛቤው ጥልቀት – ቀመሩ **ሰነፍ** በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያዊነት ዕውቅናው **ዜግነት** መሆኑ ቀርቶ **በቅድመ ሁኔታ ተገነዘ** — በገጠርና በከተማ፤ በተማረና ባልተማረ፤ በሠለጠነና ባልሰለጠነ፤ **ከአማርኛ ቋንቋ ተጨማሪ ቋንቋ በማወቅና ባለማወቅ፤** በተዕባትና በአንስት፤ በክት የዘውግ አባልነትና በዘወትረኛ፤ በአለ ዘውገኝነትና በየሉምነት፤ በማኒፌስቶ ማህበርተኝነትና በአልቦሾቹ … ምኑን እነግርሃለሁ በቃ ዜግነት በዚህና በዚያ ፍዳና አሳሩን ይከፍልልኃል።
ቁስለቱ – ያመግላል፤ መስፈሪያው – **ያበግናል። ለዕውነት ሱባዬ ያስይዛል።** የማይሰማ፤ የማይታይ የፈተና ዓይነት የለም። የኢትዮጵያዊነት አሳሩ፤ በቦንዳ፤ በደርዘን ነው። መራር ዘመን ላይ ይገኛል፤ ዓውራው ማንነት ኢትዮጵያዊነት። ስለሆነም እማም ጎዳና ላይ ስለተጣሉት ልጆቿ አምርራ – ታለቅሳለች። አብሶ ባለቤት አልቦሾቹ ይበልጡን እጅግ የበዙ ናቸው። ሰው በመጠጥና በውኃ ብቻ አይኖር ነገር …
አንተ ተፈጥሮህ አመክንዮ፤ ጉዞህ ወደ አመክንዮ። መዳረሻህም አመክንዮ። ስለምን? ሚስጢርነትህን **የመንፈስህ ብቸኛ ሚሥጢረኛ ለማድረግ ስለፈቀድክ።** በአንድ ነገር ግን መጽናናት ይቻላል። ኢትዮጵያዊነት ፈተናን አሸንፎ የተፈጠረ ሚስጢር ነውና። ወደፊትም ልብ ሞልቶ ሊያናግር የሚችለው የአመክንዮ አናት ኢትዮጵያዊነት **አሸናፊ ማንነት ሆኖ ቀጣይ መሆኑ ነው።** የሚያቆበቁቡ ማናቸውም ሳንኮች ሁሉ ከእግሩ ሥር ይነጠፋሉ። ኢትዮጵያዊነትን ተረግጦ የህዝብን ፍቅር ያፈሰ ማንም – ምንም ኃይል የለም። ወደፊትም አይኖርም። እዚህ ላይ በትልቁ የምጋራው የሊቀ – ሊቃውንቱ የታሪክ ሙሁር የፕሮፌሰር ኃይሌ ላሪቦን **„ኢትዮጵያዊነት ረቂቅ መንፈስ ነው“** ይህ አገላለጽ እኔ ሥርጉተ ሥላሴ **እንደ ዶግማ ነው የምቀበለው።** የቅኔው ንጉሥ ዬብላቴ ጌታ ሎሬት ጸጋዬ ገመድህን መንፈስም ቅመሙ ይሄው ነውና።
ስለምን? በውስጤ ያለውን ረቂቅ ሙቀቱን አሳምሬ ስለማውቀው። እሱን ሳስብ ብቻ ነው **አጃዬ** የሚሞላው። ከእሱ ጋር ለመኖር ስፈቅድ ብቻ ነው **ድንጉጥ** የማልሆነው። በየትኛውም ሁኔታና ቦታ ስለእሱ ስመሰክር ብቻ ነው መንፈሴ ከዕውነተኛው ሐሴት ጋር የሚገናኘው። ስለእሱ

ስናገር ብቻ ነው በሰው ሀገር ብኖርም ባለሀገር መሆኔ ድፍረት የሚኖረው። በሌላ በኩል በዚህ የስደት የዝንቅ ህይወት ውስጥ ከሌላ ሀገር ዜጎች ጋር በሚኖረኝ ማናቸውም ግንኙነቶች ሁሉ ንጽጽሩ በእርጋታ ሳስተውለው ረቂቁ ማንነቴ ኢትዮጵያዊነት የሰጠኝን ዝቀሽ ዕሴት ማገናዘብ ችየበታለሁና። የመሰደዴ ዋናው ተቋሜም እራሴን የምለካበት ወቄት ማግኘቴ ነው። እማላማርረውም ለዚህ ነው እንጂ፤ ለእኔ ተፈጥሮ ውጭ ሀገር **መካን** አመክንዮ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ሊገልጹት የማይችሉት **የመንፈስ እጨጌ ነው።** አውልቆ ለመኖር ቢታሰብ እንኳን – የሚስብ አንዳች ብቁ ኃይል ነገር magnet

አለው። **እህል ውሃው የማይለቅ ጥልቅ ማንነት ነው ኢትዮጵያዊነት። ወለሉ ዲካ ዬለሽ ነው። በመገፋፋት ውስጥ መቻቻልየነገሰበት። በመሸጋሸግ ውስጥ መዋህድ የተፋቀረበት።**

ኢትዮጵያዊነት ፈተናው የዘመናት ነው፤ ግን ትብትቡን ጣጥሶ **አሸናፊ ይሆናል።** እሱም እንደ እናቱ **አላዛር** ነው። ሌላው ቀርቶ ሌት ተቀን ተቀናቃኙ

እያዩለ **ስለእሱ በባለቤትነት የሚከወን የታቀደ ተከታታይ ተግባር ሳይኖር – ግን ጎልቶ፥ ፈክቶ ፥ እ ጅግም ጎልብቶ ብቅ ይላልታምረኛው – ኢትዮጵያዊነት።** ለዚህም ነው ሊቀ ሊቃውንቱ ፐ/ ኃይሌ ላሬቦ ቃል ቢያጡለት፤ መፍቻ ትርጉም ቢያጡለት **„ረቂቅ መንፈስ“**ያሉት። ረቂቅ መንፈሱን መቀበልም በቅድመ ሁኔታ ከወገብ በላይና በታች መሆን አይኖርበትም፥ ከመንገድ በላይና በታችም። „ሲወዱ እስከ ንፍጥ ልጋጉ“ ይላሉ ጎንደሬዎች ሲተርቱ። ከጋብቻ በኋላ በተጋቢ ቤተሰቦች ያለውን ትርምስ በቅኔ – ሲቃኙት። ጋብቻው ሁሉ በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ ከሆነ **የሽሪፎ ቤተኝነትን** ተከልቶ መሆን ይኖርበታል።

ስለሆነም ኢትዮጵያዊነት ሞገሴ ለሚል ተቋም፤ የፖለቲካ ድርጅት፤ ወይንም ግለሰብ ማዕቀፉ ዥንጉርጉሩንም አጽድቆ ከልብ ስለልብ **ሁነኝልሁንህ** ማለትን ይጠይቃል። **ድፍረት! ከምላስ ርጥበት ያለፈ ሁነኛ ዬማመሳከሪያ ውስጣዊ ሰነድ። ወጀብ የማይንጠው። ዬግላዊነት ቁንጥጫ የማያሸማቅቀው።**

ለዛ የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ጥልቅነቱን ለገለጸ አንደበትም፤ ዘመን አሻጋሪ ዶግማም፤ በትረ የትውልድ ሥህንም ክብሩን ቁልቁል ማውረድ ዘመንም ታሪክም ይቅር

የማይለው፤ **የህሊና ዕዳ ነው።** በተለይ „ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በክብር ትኑር!“ አቡነ ዘበሰማያቱ ወይንም „አላህ አክብር“ ላደረገ ተቋም፤ ድርጅት ወይንም የእኔ ቢጤ ባተሌ። የእግዚአብሄር ቃል „ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ „ ይላል። ለተዋህዶ አማንያን ይህን ቃለምህዳን መጋፋታም የእርግማን ጥሪትን ማጠራቀም ይመስለኛል። የጻድቃን አባቶቻችን የልፋትና የድካም ዋጋ እሾህ ሆኖ ይወጋናል።

ልዕልት ሐገራችን ኢትዮጵያ በጅምላና በችርቻሮ በንግድ የገብያ ሥርዓት የተቸረቸረች ወይንም ሱቅ ተሂዶ **የተሸመተች ሀገር አይደለችም።**ከፈጣሪ በታች ከእሷ ልቅና እና ልዕልና በላይ ማንም፥ ምንም ዬለም። ስለሆነም በእሷ የሚመጣ ጉዳይ ሁሉ፤ ከክብሯ አገላለጽ ውጪ ያሉ ጉዳዮች ሁሉ፤ እንደ አግባብነታቸው በመንፈሷ ሥር ሊተዳደሩና በቅጡ በብልጥነት ሳይሆን በብልህነትና በጥበብ ሊመሩ ይገባል። ንጉሥ ዳዊት „ዬቤትህ ቅናት በላይ“ ያለው ይፈጸም ዘንድ – ዶግማውን መፍቀድ ይኖርብናል። **ዬቤቷ ቅናት ሊያርመጠምጠን ይገባል።** ጊዜ ያልፋል፤ ዘመን ያልፋል፤ ትውልድም ያልፋል። **ኢትዮጵያ ግን ፈጽሞ**

**አታልፍም። ለዘለዓለም ትኖራለች! አልፋና ኦሜጋ ናት። ትምክኽቷ አምላኳ ነውና።**

**ኢቲዮጵያዊነት መሸፈኛ፤ መጠቅለያ፤ ማሸጊያ ወረቀት መሆን አይኖርበትም።** የልብ ክፍል፤ የኩላሊት ክፍል፤ ቤተ – ትልቅና ትንሽ አንጀት – ዓይው ጭንቅላት ወዘተ … ሁሉም በአንድ ላይ በተፈጥሮ ሥርአታቸው ተግባራቸውን ሲወጡ ብቻ ነው ሰውም እንደሰው፤ ትውልድም እንደትውልድ የሚቀጥለው። ስለሆነም በኢትዮጵያዊነት ውስጥም የላይ ቤት፥ የታች ቤት ሠርቶ ስብከት ለእኔ የእንቧይ ቤት

ነው። **በመሆንየከበረ ኢትዮጵያዊነት ነው ነፍስን ሊገዛና ሊነዳ የሚችለው።** እንደ ጌታ ብላቴ ሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድህን – **መሆን መቻል።**

ጌታ ብላቴ ሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድህን ከሊቅ እስከ ደቂቅ መንፈሱ ክብር ያልሰጠበት፤ ከውስጡ ያልተመሰጠበት ከቶ አንዳችም ብሄራዊ ጉዳይ ሆነ ማህበረሰብ የለም። **ለዛውም ሰውንና ዕውነትን ማዕከል በማድረግ።** ዛሬ በዘመናችን በኢትዮጵያዊነት አመክንዮ ውስጥ ለእኔ ለሥርጉተ ሥላሴ ናሙና የምለው የስሜን አሜሪካ ዬስፖርት ፌስቲባል መሰናዶና ዕሴቱን ብቻ ነው። ወጣ ገባ አይደለም። ቀጥ ባለ ግልጽና ቀጥተኛ አቋም በየዓመቱ ብሄራዊ ሰንደቅዓላማችን ከፍ እንዲል ያደርጋል። ይህ **የሰንደቅ ተጋድሎ ገድል ነው** ለእኔ። ተቋሙ በብሄራዊ ዓርማችን ላይ ያለው ምራቁን የዋጠ አቋም በውስጣችን ያለውን አክብሮትና ልቅና ገላጭ – **የታሪካችን ቁንጮ** ነው ማለት ያስችለኛል። ለእኔ ለሥርጉተ ሥላሴ የስሜን አሜሪካው ዓመታዊ የስፖርት ዝግጅት **አድዮ አበባ** ነው። ለእኔ የኢትዮጵያዊነት አዝመራ ነው። ለእኔ ባለቅኔው ጸጋዬ ገመድህን ነው። ለእኔ ጀግና አብዲሳ አጋ ነው። በአጋጣሚው ያለኝን የውስጥ ፍቅር ስገልጽ ለአዘጋጆች በሐሴት ነው።

**እርገት።**

በል የእኔ አባታዊ ዬሥነ ጥበብ ጌታ ጋሼ ጸጋዬ ልሰናበትህ ስለእናታችን እንወዛወዝልህአለን የንፋስ ፍጥነት መለኪያው Anemometer እንዲህና እንዲያ …

ማጠናከሪያ ጹሁፍ

http://www.zehabesha.com/amharic/?p=39302

የውስጥ እንደራሴ – እንደ ህዝብ … – ሥርጉተ ሥላሴ

**ኢትዮጵያዊነት ይከበር!**

መሸቢያ ጊዜ። እግዚአብሄር ይስጥልኝ።

Ethiopatriots.com